# አራዳ እንዲህ ነው

ካራዳ ልጅ ጋራ ጨዋታ
መች ይጠገብና ያለው ደስታ
ካራዳ ልጅ ጋራ ፍቅር
ተይው አይወራ ይቅር
ላፈቀረው እሚሞት እሚታመን
ባቶጂው ነበረ የሚገርመን
ሁሉንም የሚያየው በፍቅር ነው
ያራዳ ልጅ ማለት እንደዚህ
እንደዚህ ነው አራዳ አንዲህ ነው
እንደዚህ ነው ነይ ዘመድ አለም
እንደዚህ ነው እንዳራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ቀና ሰው የለም
እንደዚህ ነው አይገኝም እንጂ
እንደዚህ ነው እንዲህ በቀላል
እንደዚህ ነው ምርጥ ያራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ምኑ ይጠላል።
ሲያገኝ አይኮፈስም ሲያጣም አይጨንቀውም
ሀብት ዝና ስልጣን አያስገርመውም
ምን ታረጊዋለሽ ባራዳ ልጅ አለም
ቅንነት ይበዛል ሃሜት ተንኮል የለም
እከሌ አተረፈ ይሁንለት ብሎ
ለእከሌ ሲሳካ ያድርግለት ብሎ
ለማንኛውም ሠው የሚመኘው ጥሩ
ጎረቤቱ መውደድ ፍቅር ነው እድሩ
ደግ ደጉን እንጂ አያውቅ ምቀኝነት
ክፋትን አርቆ ሚኖር በቅንነት
ይሄነው ትርጉሙ ያራዳ ልጅ ማለት።
እንደዚህ ነው አራዳ እንዲህ ነው

እንደዚህ ነው ስሚኝ ዘመዴ
እንደዚህ ነው ለሰው ይሞታል
እንደዚህ ነው ካፈቀረ አንዴ
እንደዚህ ነው አይገኝም እንጂ
እንደዚህ ነው እንዲህ በቀላል
እንደዚህ ነው ምርጥ ያራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ምኑ ይጠላል።
=============================

ካራዳ ልጅ ጋራ ጨዋታ
መች ይጠገብና ያለው ደስታ
ካራዳ ልጅ ጋራ ፍቅር
ተይው አይወራ ይቅር
ክፋት ምቀኝነት መችያውቅና
ወሬና አሉባልታ መችያውቅና
ሲጠላም ሲወድም ፊትለፊት ነው
ያራዳ ልጅ ማለት እንደዚህ ነው

እንደዚህ ነው አራዳ እንዲህ ነው
እንደዚህ ነው ነይ ዘመድ አለም
እንደዚህ ነው እንዳራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ቀና ሰው የለም
እንደዚህ ነው አይገኝም እንጂ
እንደዚህ ነው እንዲህ በቀላል
እንደዚህ ነው ምርጥ ያራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ምኑ ይጠላል።

በዚህ ክፉ ዘመን ስስት በበዛበት
ሌባ ማፈር ትቶ በሚጀነንበት
የሃሰት ነቢያት እጅግ በበዙበት
አረመኔው ደፍሮ አማኝ ነኝ ባለበት
ሞትን ንቆ ጥሎ ሒይወት ያከበረ
እኔ ልሙት ብሎ ሌላ ሠው ያኖረ

አምላኩን ተማምኖ መች ይፈራል ሞት
በፍቃዱ አይተናል ያራዳን ሒይወት
ለኔ ማለት ትቶ ለኛ እሚል ሲመጣ
ራሱን ያሸነፈ ስስትን የረታ
ፍቃዱን አብዛልን የላይኛው ጌታ
እንደዚህ ነው አራዳ አንዲህ ነው
እንደዚህ ነው ነይ ዘመድ አለም
እንደዚህ ነው እንዳራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ቀና ሰው የለም
እንደዚህ ነው አይገኝም እንጂ
እንደዚህ ነው እንዲህ በቀላል
እንደዚህ ነው ምርጥ ያራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ምኑ ይጠላል።

ከወንዝ ልጅነት ይርቅ ይዘልና
ከዘር ከሃይማኖት ከጎሳ ይወጣና
ሠው ሠው ነው በማለት ማሰብ እሚጀምረው
ሁሉኑም የሰው ልጅ አንድ አርጎ እሚቆጥረው
ማንም ይሁን ማንም ብቻ ይሁን ጥሩ
ከየትም ይምጣ ከየት ብቻ ይሁን ጥሩ
መች ያስፈልግና ብሔርና ዘሩ
ያራዳ ልጅ ይላል ዋናው ነገር ፍቅሩ
የሚያመሳስለው አለው ብዙ ነገር
ህይወቱን ይሰጣል ላመነበት ነገር
አይደራደርም በናቱና ባገር
እንደዚህ ነው አራዳ እንዲህ ነው
እንደዚህ ነው ነይ ዘመድ አለም
እንደዚህ ነው እንዳራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ቀና ሰው የለም
እንደዚህ ነው አይገኝም እንጂ

እንደዚህ ነው እንዲህ በቀላል
እንደዚህ ነው ምርጥ ያራዳ ልጅ
እንደዚህ ነው ምኑ ይጠላል።

Last modified: 6:50 AM